# የ Coronavirus (Covid19) መመርያ

**አማርኛ / Amharic**

COVID-19 ሳንባ እና የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቃ አዲስ በሽታ ነው። ኮሮና ቫይረስ በሚባል ቫይረስ የሚከሰት ነው።

እንደ፡

- ከፍተኛ ሙቀት – ደረትዎን ወይም ጀርባዎን ሲነኩ ከፍተኛ ሙቀት ይሰማዎታል
- አዲስ ተከታታይ የሆነ ሳል ካለብዎ – በተደጋጋሚ ማሳል ጀምረዋል ማለት ነው

በቤትዎ መቆየት አለብዎ።

## ቤት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ መቆየት?

- ምልክቶቹ ያለበት ማንኛውም ሰው በቤት ውስጥ ቢያንስ ለ 7 ቀን መቆየት አለበት።
- ከሌላ ሰው ጋር የሚኖሩ ከሆነ ኢንፌክሽኑን ከቤት ውጭ እንዳይሰራጭ ለማድረግ እነሱም ቢያንስ ለ 14 ቀናት ቤት ውስጥ መቆየት አለባቸው።
- ከ 14 ቀናት በኋላ ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው ምልክቶቹ ከሌሉበት ወደ ተለመደ ተግባራቸው መመለስ ይችላል።
- ነገር ግን በቤትዎ ያለ ማንኛውም ሰው እነዚህ ምልክቶች ካሉበት፣ ምልክቱ ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ለ 7 ቀናት በቤት ውስጥ መቆየት አለበት። ይህም ቤት ውስጥ ከ 14 ቀናት በላይ ቢቆይም ማለት ነው።
- 70 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው ፣ ለረጅም ጊዜ የቆየ የጤና እክል ያለባቸው፣ ነብሰ ጡር የሆኑ ወይም የደከመ በሽታ የመከላከል አቅም ያላቸው ሰው ጋር አብረው የሚኖሩ ከሆነ ለ 14 ቀናት መቆየት የሚችሉበት ሌላ ቦታ ይፈልጉላቸው።
- በቤት ውስጥ አንድ ላይ መቆየት ካለብዎ፣ በተቻለ መጠን ተራርቀው ለመቆየት ይሞክሩ።

[ቤት ውስጥ ስለመቆየት ምክር]

| | | |
|---|---|---|
|  ወደ ሥራ፣ ትምህርት ቤት፣ GP ቀዶ ጥገና፣ ፋርማሲ ወይም ሆስፒታል አይሂዱ |  የተለያዩ መገልገያዎችን ይጠቀሙ፣ ወይም ከተጠቀሙ በኋላ ያጽዱ |  ከሰዎች ጋር ቅርብ ንክኪን ያስወግዱ |
|  ምግብ እና መድኃኒት እርስዎ ያሉበት ቦታ ድረስ እንዲመጣልዎ ያድርጉ |  ጎብኚዎች አይኑርዎት |  ከተቻለ ለብቻዎ ይተኙ |
|  እጅዎን በየጊዜው ይታጠቡ |  ብዙ ውሃ ይጠጡ |  ምልክቶቹን እንዲያስታግስልዎ ፓራሲታሞል ይውሰዱ |

In association with British Red Cross

Doctors of the World

## NHS 111 ን ማግኘት ያለብኝ መቼ ነው?

- ካመምዎና  ቴሌቪዥን ማየት፣ ስልክዎን መጠቀም፣ ማንበብ ወይም ከአልጋ መነሳት የመሳሰሉ ለወትሮ የሚያደርጓቸውን ነገሮች ማከናወን ካልቻሉ
- ቤት ውስጥ ሆነው ምልክቶቹን መቋቋም ካቃትዎ
- ህመምዎ እየባሰ ከሄደ
- ምልክቶቹ ከ 7 ቀናት በኋላ እየቀነሱ ካልሄዱ

## NHS 111 ን እንዴት ነው የማገኘው?

ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ለማወቅ የ **NHS 111 ኦንላይን ኮሮና ቫይረስ አገልግሎት** መጠቀም ይችላሉ። ኦንላይን አገልግሎቶችን መጠቀም ካልቻሉ 111 (ይህ ነጻ የጥሪ መስመር ነው) ላይ መደወል ይችላሉ ። የቋንቋዎ አስተርጓሚ መጠየቅ ይችላሉ።

## ስለ ስደተኝነት ሁኔታዬ ስጋት ካለብኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ሁሉም የኮሮና ቫይረስ የ NHS አገልግሎቶች በዩኬ ውስጥ ያላቸው የስደተኝነት ሁኔታ ግምት ውስጥ ሳይገባ ለሁሉም በነጻ የሚሰጡ ናቸው። ይህም ውጤቱ ነጌቲቭ ቢሆንም የኮሮና ቫይረስ ምርመራ እና ህክምናን ያጠቃልላል። የ COVID-19 ምርመራ ወይም ህክምና ለሚደረግላቸው ሰዎች የስደተኝነት ሁኔታ ማጣራት እንደማያስፈልግ ለ NHS ሆስፒታሎች ተነግሯቸዋል።

## ኮሮና ቫይረስ እንዳይሰራጭ ለማገዝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

- እጅዎን  በሳሙና እና በውሃ ቢያንስ ለ 20 ሰከንድ ቶሎ ቶሎ ይታጠቡ
- ቤት ውስጥ ስለመቆየት የተሰጥዎ ምክርን ይከተሉ

ይከ ምክር የተሰጠው በ NHS የጤና ምክር እና መረጃ መሰረት ሲሆን የመጡበት ሃገር ግምት ውስጥ ሳይገባ ለሁሉም ሰው የተሰጠ ምክር ነው። ለበለጠ መረጃ:

- የ NHS መመርያ: **https://www.nhs.uk/conditions/coronavirus-covid-19/**

እትም 2 [16.03.2020]

Version 2 [16.03.2020]